# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ

## በኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ ወርሃዊ መፅሔት

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
Addis Ababa Design & Construction Works Bureau

## የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ

### እንኳን ደስ አላችሁ፤ እንኳን ደስ አለን!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2015 በጀት ዓመት በአንፃራዊ የተሻለ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ክፍለከተሞች፣ የካቢኔ አባል ለሆኑ እና የካቢኔ አባል ላልሆኑ ሴክተሮች ዕውቅና ሰጥቷል።

በዚህም መሰረት የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ባሳለፍነው በጀት ዓመት የካቢኔ አባል ከሆኑ ሴክተሮች ውስጥ የተሻለ አፈፃፀም በማስመዝገብ የ2ኛነት ደረጃን በመያዝ ከአስተዳደሩ ዕውቅና ተበርክቶለታል።

በዚህ ስኬት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ለነበራቸው ትጉሀን የተቋሙ ሰራተኞች፣ ለቢሮው ማኔጅመንት አባላት እንዲሁም አጋር አካላት ውጤቱ የጋራ በመሆኑ ቢሮው የእንኳን ደስ ያለን መልዕክቱን ያስተላልፋል።

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ**
**ለከተማችን መሻሻል እንሰራለን!!!!**
**Dedicated for the betterment of our City!!!!**






# ቢሮው አገልግሎቶቹን ለማዘመን የሚያስችሉ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።



የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ተልዕኮዎቹን በማሳካት ሂደት ውስጥ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ለማዘመን የሚያስችሉ ስራዎች እያከናወነ ይገኛል።

ቢሮው ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ የሆነውን ወቅታዊ የግንባታ ግብዓት ዋጋ ጥናት ዲጂታላይዝ ለማድረግ በሚችልበት አግባብ ዙሪያ ቴክኖሎጂ አቅራቢ ከሆነው ከህሱድ ቴክኖሎጂ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ጋር ውይይት አድርጓል።

ድርጅቱ Gebeya X በተሰኘው ዲጂታል የግብይት ፕላትፎርሙ የቢሮውን ወቅታዊ የግንባታ ግብዓት ዋጋ ተከላውን በዘመነ መልኩ ለማቅረብ በሚቻልባቸው አግባቦች ዙሪያ የቢሮው አመራሮችና የድርጅቱ ተወካዮች በተገኙበት ውይይት ተደርጓል።በውይይቱ ወቅት የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኃላፊ ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም እንዳሉት ቢሮው ከመቼውም ጊዜ በላይ ዲጂታላይዜሽንን በተቋሙ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን በስፋት እያከናወነ እንደሚገኝ ጠቅሰው ከነዚህ ተግባራት ውስጥም የጨረታ ሂደቱን፣የኮንትራት አስተዳደር ስራዎቹን፣ የፕሮጀክት ማኔጅመንት ስርዓቱን እንዲሁም የፋይል አስተዳደሩን ለማዘመን የተሄደበትን ርቀት በማስረዳት የዛሬው ውይይትም የግንባታ ግብዓት ዋጋ ጥናት ስራውን በማዘመን ረገድ የሚያመጣው ውጤት የሕብረተሰቡን ብሎም የቢሮውን ተጠቃሚነት እንደሚያረጋግጥ ሲታመንበት ወደተግባር እንደሚገባ ጠቁመዋል ።

ቢሮው በዓዋጅ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሰረት በየሩብ ዓመቱ ወቅታዊ የግንባታ ግብዓት ዋጋ ጥናት በማጥናት እንደሚያቀርብ ይታወቃል።

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ
ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ጥቅምት 29/2016 ዓ/ም

# ቋሚ ኮሚቴው የቢሮውን የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች ገመገመ።





በአዲስ አበባ ከተማ ምክርቤት የከተማ ልማት፣ኮንስትራክሽንና አካባቢ ጥበቃ ቋሚ ኮሚቴ የቢሮውን የ2016 በጀት ዓመት ዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች ገምግሟል።

በጊዜ ማዕቀፉ በቢሮው የነበሩ ከዋና እና ከደጋፊ ዕቅዶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣ከአገልግሎት አሰጣጥ እንዲሁም ከሪፎርም ስራዎች ጋር የታዩ አፈፃፀሞች የኮሚቴው የትኩረት አቅጣጫዎች የነበሩ ሲሆን በነዚህና በሌሎችም ነጥቦች ዙሪያ የታዩ ክፍተቶች እና ጥንካሬዎች በዝርዝር ታይተዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ኒዕመተላኽ ከበደ በግምገማው ማጠቃለያ ላይ ባደረጉት ንግግር ቢሮው ባስመዘገበው አፈፃፀም ከከተማ አስተዳደሩ የተደረገለትን ዕውቅና አስመልክተው የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክታቸውን በማስቀደም እየተሰሩ የሚገኙ ስራዎች የከተማዋን ገፅታ በመቀየር እንዲሁም መንግስትና ህዝብን ድልድይ ሆነው በማገልገል ረገድ ትልቅ ድርሻ እየተወጡ እንደሚገኙ ጠቅሰው ተቋሙ የተሰጡትን አስተያየቶች እንደ ግብዓት በመውሰድና መስተካከል ያለባቸውን ስራዎች በፍጥነት በማስተካከል የተሻለ አፈፃፀም ለማስመዝገብ መስራት እንዳለበት አሳስበዋል።

የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኃላፊ ኢ/ር አያልነሽ ሐብተማርያም በበኩላቸው ቢሮው ላስመዘገበው ውጤት እንዲሁም ያንን ተከትሎ ለተደረገለት ዕውቅና የተቋሙ አመራርና ሰራተኞች ጥረት ውጤት ብቻም ሳይሆን የሌሎች አጋሮች በተለይም የቋሚ ኮሚቴው ድጋፍና ክትትል ቀላል የማይባል መሆኑን ጠቅሰው ኮሚቴው ለበነረው ያልተገደበ እገዛ በቢሮው ስም ምስጋናቸውን በማቅረብ ከኮሚቴው የተነሱትን እያንዳንዱን ሀሳቦች በመውሰድና በማረም የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ቢሮው በትኩረት ይሰራል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
Addis Ababa Design & Construction Works Bureau

**የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት**

**ጥቅምት 29/2016 ዓ/ም**

# የቢሮው ሰራተኞች የሳይንስ ሙዚየምን ጎበኙ





**የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ሰራተኞች ከመስከረም 29/2016 ጀምሮ እስከ ጥቅምት 28/2016 በቱሪዝም ሚኒስቴር በተዘጋጀውና በሳይንስ ሙዚየም በሚካሄደው ሀገር-ዓቀፍ የቱሪዝምና የሆስፒታሊቲ ኤግዚቢሽን ላይ ተገኝተው ጉብኝት አካሂደዋል። በጉብኝቱ የተሳተፉ የተቋሙ ሰራተኞች በፈጠራ፣በባህልና በህብረ-ብሄራዊ ስብጥሩ የሀገራችን ተምሳሌት ሆኖ የተደራጀውን የሳይንስ ሙዚየምን መጎብኘታቸው የፈጠረባቸውን ስሜት በመግለፅ መሰል ሁነቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ሲሉ ተደምጠዋል።**

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
Addis Ababa Design & Construction Works Bureau

SUBSCRIBE

Ahttps://www.facebook.com/AddisConstruction.com
https://t.me/AddisCityCon
https://twitter.com/AddisCityhttps://twitter.com/AddisCity
https://www.youtube.com/channel/UCwuES6TQUZmVlUT8tazLHmg

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ጥቅምት 19/2016 ዓ/ም

# የኮሚሽኑ ህንፃ በቅርቡ ተጠናቆ ለአገልግሎት ዝግጁ ይደረጋል።



የጀሞ ቁጥር 01 የእሳትና አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን G+4 ህንጻ ፕሮጀክት በሚቀጥሉት ሳምንታት ተጠናቆ የታለመውን አገልግሎት መስጠት ይችል ዘንድ በከፍተኛ ትኩረት እየተከናወነ ይገኛል።

የአዲስ አበባ  የእሳትና አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በከተማዋ በየጊዜው የሚከሰቱትን ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ለመቀነስ የሚያስችሉ መሰረተ-ልማቶችን በተለያዩ ክፍለከተሞች  በማስፋፋት የህብረተሰቡን ተጋላጭነት ብሎም ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችሉ  ስራዎችን እየሰራ  ይገኛል።

ከነዚህ የተቋማት ግንባታዎች ውስጥ የሚጠቀሰውና በአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ባለቤትነት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ ወረዳ 11 በ4080 ካ.ሜ. ቦታ ላይ የላፍቶ አትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ ማዕከልን ተዋስኖ እየተገነባ የሚገኘው  የጀሞ ቁጥር 01 የእሳትና አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ባለ 5 ወለል ህንጻ የማጠናቀቂያ ስራዎች እየተሰሩለት ይገኛል።

96 በመቶ ፊዚካል አፈፃፀም ላይ የደረሰውንና ከ225 ሚሊዮን ብር በላይ የውለታ መጠን የተያዘለትን ይህን ፕሮጀክት ታቡ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማ በስራ ተቋራጭነት እንዲሁም ስኬል አማካሪ አርክቴክቶችና መሀንዲሶች በአማካሪነት እያከናወኑት የሚገኝ ሲሆን በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ይጠናቀቅ ዘንድ በምሽት ፈረቃ ጭምር ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል።

አሁን ላይ በግንባታ ሳይቱ የምድረ-ጊቢ ሰብ ቤዝ ስራ፣የአጥር ስራ፣የመጫወቻ ሜዳ ስራ እንዲሁም የውጪ መታጠቢያ ቤቶች ስራዎች እየተከናወኑ ሲሆን በቀጣይ የምድረ-ጊቢ አስፋልት ስራ፣የአጥር ቀለም ስራ፣የመጫወቻ ሜዳ ማጠናቀቅና ሌሎች የማጠቃለያ እንዲሁም የፅዳት ስራዎች እንደሚከናወኑ የተያዘው መርኃ-ግብር ያሳያል።

SUBSCRIBE

Ahttps://www.facebook.com/AddisConstruction.com
https://t.me/AddisCityCon
https://twitter.com/AddisCityhttps://twitter.com/AddisCity
https://www.youtube.com/channel/UCwuES6TQUZmVlUT8tazLHmg

የአዲስ አበባ ዲ ንና ግንባታ
ስራዎች ቢሮ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች
ዳይሬክቶሬት

ጥቅምት 16/2016 ዓ/ም

# የቢሮው የዝግጅት ምዕራፍ አፈፃፀም ምዘና ተካሄደ።







የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ በ2016 በጀት ዓመት የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮን የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎች የቢሮውና የዘርፍ ኃላፊዎች እንዲሁም ዳይሬክተሮች በተገኙበት ገምግሟል።
ምዘናው ቢሮው በበጀት ዓመቱ ለማከናወን ያቀደውና በተግባር ያከናወነውን አፈፃፀም ታሳቢ ያደረገ ሲሆን በአጠቃላይ በጊዜ ምዕራፉ የቢሮው ዕቅድ እስከ ባለሙያ ስለመውረዱ እና ውይይት ስለመደረጉ፣በቢሮው ውስጥ የሌብነት እና ብልሹ አሰራሮች በመታገል ዙሪያ ስለተሰሩ ስራዎች እና ልዩ ልዩ አደረጃጀቶች የውይይት ሂደትን በተመለከተ፣ከባለድርሻ አካላት ጋር ስለተተደረጉ የስራ ግንኙነቶች እና አጠቃላይ የደንበኞች ፈጣን አገልግሎት አሰጣጥ ስርአት ስለመዘርጋቱ፣በቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በስታንዳርድ ምዝገባዎች እና የሰው ሀይል ማብቃት ዙሪያ ያተኮረ ሲሆን የነበሩ ስኬቶች እና ውሱንነቶች

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
Addis Ababa Design & Construction Works Bureau

SUBSCRIBE

Ahttps://www.facebook.com/AddisConstruction.com
https://t.me/AddisCityCon
https://twitter.com/AddisCityhttps://twitter.com/AddisCity
https://www.youtube.com/channel/UCwuES6TQUZmVlUT8tazLHmg

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ጥቅምት 16/2016 ዓ/ም

# የህፃናትና ወጣቶች ቴአትር ምዕራፍ 3 ስራዎች ዲዛይን ግምገማ ተካሄደ።





በቂርቆስ ክፍለከተማ በተለምዶ ፍላሚንጎ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ እየተገነባ በሚገኘው ባለ 13 ወለል ህንፃ የመጨረሻ ስራ የሆነው የምዕራፍ 3 ስራዎች ዲዛይን ግምገማ አራቱም አካላት በተገኙበት ተገምግሟል።

የፕሮጀክቱ አሰሪ መስሪያ ቤት የሆነው የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ፣የመጨረሻ ተጠቃሚ የሆነው ተቋም የአዲስ አበባ ባህል፣ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ፣ስራ ተቋራጩ ኢምፕረሽን ጠቅላላ ንግድ ኃ/የተ/የግ/ማ እንዲሁም አማካሪ ድርጅቱ ዮሀንስ አባይ አማካሪ ድርጅት በተሳተፉበት በዚህ የግምገማ መድረክ በአማካሪ ድርጅቱ የተዘጋጀው ዲዛይን ቀርቦ የተገመገመ ሲሆን ወደቀጣይ ስራ ለመግባት የሚያስችሉ ሀሳቦችና አቅጣጫዎች ከፕሮጀክቱ ተዋናዮች ተሰንዝረዋል።

የዚህ ፕሮጀክት ሶስተኛ ምዕራፍ ስራ 1200 ተመልካቾችን የመያዝ ዓቅም ያለውን ቤተ-ተውኔት ጨምሮ እጅግ በቴክኖሎጂ የተደራጁ 2 ሲኒማዎች፣በግብዓት የተሟላ የህፃናት መጫወቻ( Game zone ) እንዲሁም ዘመኑን የዋጁ ተያያዥ ኤሌክትሮ ሜካኒካል ስራዎችን ያካትታል።

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
Addis Ababa Design & Construction Works Bureau

SUBSCRIBE

Ahttps://www.facebook.com/AddisConstruction.com
https://t.me/AddisCityCon
https://twitter.com/AddisCityhttps://twitter.com/AddisCity
https://www.youtube.com/channel/UCwuES6TQUZmVlUT8tazLHmg

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ጥቅምት 13/2016 ዓ/ም

# ቢሮው ከተጠሪ ክፍለከተማ ፅ/ቤቶች ጋር የስምምነት ሰነድ ተፈራረመ፡፡





**የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ በክፍለከተማ ከሚገኙ የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ፅ/ቤቶች ጋር በ2016 በጀት ዓመት የያዛቸውን ዕቅዶች በጋራ ለመስራት የሚያስችለው የስምምነት ሰነድ ተፈራረመ፡፡ ቢሮው የክፍለከተሞችን የ2016 በጀት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም በገመገመበትና የ2016ን ዕቅድ ለመፈፀም የሚያስችለው ስምምነት በተፈራረመበት በዚህ መድረክ ሁሉም ክፍለከተሞች በሩብ ዓመቱ የነበራቸውን የተግባር አፈፃፀም አቅርበው ግምገማ የተደረገ ሲሆን እንደ አጠቃላይ የነበሩ ተግዳሮቶች በዝርዝር ቀርበው ለቀጣይ የተግባር ምዕራፍ ስራዎች የሚሻሻሉበት ምክረ-ኃሳቦች ተንሸራሸረዋል፡፡**

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
Addis Ababa Design & Construction Works Bureau

Ahttps://www.facebook.com/AddisConstruction.com
https://t.me/AddisCityCon
https://twitter.com/AddisCityhttps://twitter.com/AddisCity
https://www.youtube.com/channel/UCwuES6TQUZmVlUT8tazLHmg

SUBSCRIBE

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ጥቅምት 13/2016 ዓ/ም

# 511 አልጋዎች ያሉት የጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል ማስፋፊያ ፕሮጀክትን ለማጠናቀቅ የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል።





የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ እያከናወናቸው ከሚገኙ ግዙፍ የጤና መሰረተልማት ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ የሆነውና የጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል ማስፋፊያ ፕሮጀክት በዚህ ዓመት መጨረሻ ተጠናቆ የታለመለትን አገልግሎት መስጠት እንዲችል እየተሰራ ይገኛል።

በ6,310 ሜ ስኩዌር ቦታ ላይ ያረፈውና ከ656 ሚሊዮን ብር በላይ ተመድቦለት በብርሀን ጦቢያው ሕ/ስ/ተ ስራ ተቋራጭነት እንዲሁም በስኬል አማካሪ አርክቴክቶችና መሀንዲሶች አማካሪነት አእየተገነባ የሚገኘው ይህ ባለ 9 ወለል ህንፃ 40 በመቶ ፊዚካል አፈፃፀም ላይ የደረሰ ሲሆን በተሰጠው የጊዜ ማዕቀፍ ለማጠናቀቅ የሚያስችሉ ስራዎች እየተከናወኑለት ይገኛል።

በሆስፒታሉ 67 አልጋዎች የሚይዙ 10 የፅኑ ህሙማን መታከሚያ ክፍሎችን ጨምሮ 6 የቀዶ ጥገና ክፍሎች፣12 የነርሶች ክፍል፣2 የለይቶ ማቆያ ክፍሎች፣የ ሲቲ ስካን፣ አልትራሳውንድ ፣የራጅ እና የኤም.አር.አይ ክፍሎች እንዲሁም ለህክምናው አስፈላጊ መሰረተልማቶች ጥራታቸውን ጠብቀው የሚገነቡለት ይሆናል።

ይህ ሆስፒታል ሲጠናቀቅ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የመጣውን የድንገተኛ አደጋዎች ህክምና በልዩነት እንዲሰጥ ታልሞ እየተገነባ ሲሆን በዚህ ረገድ የሚስተዋለውን ችግር በእጅጉ ይቀርፋል ተብሎ ይጠበቃል።

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
Addis Ababa Design & Construction Works Bureau


Ahttps://www.facebook.com/AddisConstruction.com
https://t.me/AddisCityCon
https://twitter.com/AddisCityhttps://twitter.com/AddisCity
https://www.youtube.com/channel/UCwuES6TQUZmVlUT8tazLHmg

SUBSCRIBE


የአዲስ አበባ ዲ[...]ንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

ጥቅምት 06/2016 ዓ/ም

# በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለከተማ ከ80 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸው ፕሮጀክቶች ተመርቀው ለአገልግሎት ክፍት ተደረጉ።










**ክፍለከተማው በ3ኛው ዙር የ90 ቀናት ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ጃንጥራት አባይ በተገኙበት በዛሬው ዕለት በይፋ አስመርቋል ።**

**በዛሬው ዕለት በይፋ ከተመረቁት ፕሮጀክቶች ውስጥ የወረዳ 2 ዩኒሳ አደባባይ ማስዋብና ማልማት፣ የወረዳ 9 የመስሪያ ቦታ ሼድ እንዲሁም የመልካ ጨፌ ፖሊስ ጣቢያ የሚጠቀሱ ሲሆን ለፕሮጀክቶቹ መሳካት የፋይናንስ ድጋፍ ላደረጉ የልማቱ አጋሮች ከክፍለከተማው ዕውቅና ተበርክቶላቸዋል።**

Ahttps://www.facebook.com/AddisConstruction.com
https://t.me/AddisCityCon
https://twitter.com/AddisCityhttps://twitter.com/AddisCity
https://www.youtube.com/channel/UCwuES6TQUZmVlUT8tazLHmg

SUBSCRIBE

የአዲስ አበባ ዲ[illegible]ንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

ጥቅምት 05/2016 ዓ/ም

# የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ አመራሮች እና ሰራተኞች የሰንደቅ ዓላማ በዓልን አከበሩ።





**የአዲስ አበባ ከተማ የዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ አመራሮች እና ሰራተኞች ጋር በጋራ በመሆን 16ኛውን የሰንደቅ-ዓላማ ቀን አክብረዋል።**

**በዓሉን በስራ ቦታቸው ጊቢ ውስጥ አመራሮች እና ሰራተኞች ባሉበት የኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር በመዘመር፣ የአንድነታችን ዓርማ የሆነውን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በክብር በመስቀል አክብረዋል።**

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ
Addis Ababa Design & Construction Works Bureau

Ahttps://www.facebook.com/AddisConstruction.com
https://t.me/AddisCityCon
https://twitter.com/AddisCityhttps://twitter.com/AddisCity
https://www.youtube.com/channel/UCwuES6TQUZmVlUT8tazLHmg

SUBSCRIBE

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ስራዎች ቢሮ ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ጥቅምት 05/2016 ዓ/ም